5

በትራንስፖርት ሚኒስቴር
የትራንስፖርት ባለሥልጣን

የተሻሻለ
የመናኸሪያ ባለቤትነትና ግንባታ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አገር አቀፍ መመሪያ

678/2013

የካቲት/2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ

ክፍል አንድ

1. መግቢያ

በአገራችን የመናኸሪያዎች አደረጃጀት፣ አሠራርና አገልግሎት አሰጣጥ ከቦታ ቦታ የተለያየ በመሆኑ ኅብረተሰቡ ሥርዓት ያለውና ወጥ የሆነ አገልግሎት እንዳያገኝ አድርጐታል። አሠራርና አስተዳደሩም ብቃትና ጥራት የነበረው አይደለም።

በመናኸሪያዎችም የነበረው የትራንስፖርት አገልግሎት አሰጣጥ ለሕገ-ወጥ ደላላዎችና ወያላዎች እንዲሁም ጋዋን ለባሾች አመቺ ሁኔታ የፈጠረና ተገልጋዩ ኅብረተሰብ ለወከባና እንግልት የተዳረገ ሆኖ ከመቆየቱ በላይ የባለሀብቱን ተጠቃሚነትም ያረጋገጠ አልነበረም። ለዚህም እንደ ምክንያት የሚጠቀሰው መናኻሪያዎችን በባለቤትነት የሚያስተዳድረው አካል ለሥራው ቀረቤታ ያልነበረው በመሆኑ ነው።

በመሆኑም በመላው አገሪቷ የሚገኙ ሥራ ላይ የዋሉና በአዲስ የሚገነቡ መናኸሪያዎች ወጥ የሆነ አጠቃቀም፣ አስተዳደርና ባለቤትነት ያላቸውና ከማንም ጣልቃ ገብነት የፀዳ ሆኖ በፌዴራል ወይም በክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም ቢሮዎች እየተመሩ የአገልግሎት አሰጣጣቸው ደረጃውን የጠበቀና ውጤታማ እንዲሆን መደረግ ይኖርበታል።

በየትኛውም ደረጃ የሚገኙ መናኸሪያዎች አሠራርና አገልግሎት አሰጣጥም ብቃት ባለው የሰው ኃይልና በዘመናዊ የሥራ መሣሪያዎች የተደራጀ በአሠራር ደንብና መመሪያ የተደገፉ መሆን አለባቸው።

በአጠቃላይ አሁን ያለትን የአደረጃጀት፣ የአሠራርና አገልግሎት አሰጣጥ ችግርችን በመፈተሽ መናኸሪያዎችን በአዲሱ መሠረታዊ የአሠራር ሂደት ለውጥ በተቃኘና የተገልጋዩ ሕዝብ ፍላጐት ሊያረካ በሚያስችል ሁኔታ እንዲሁም በዘርፉ የተሠማሩ ወደፊትም ሊሠማሩ የሚችሉ ባለሀብቶችን በሚያበረታታ አግባብ ወጥነት ያለው የአሠራር መመሪያ ማውጣት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ይህ የመናኸሪያዎች ባለቤትነትና ግንባታ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አገር አቀፍ የአሠራር መመሪያ ተዘጋጅቷል።

2. <u>ርዕስ</u>

ይህ መመሪያ "የመናኸሪያ ባለቤትነትና ግንባታ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም አገር አቀፍ መመሪያ" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

3. <u>ትርጓሜ</u>

3.1. *"የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያ"* ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች መነሻና መድረሻ ጣቢያ ሲሆን፣ የሥምሪት አገልግሎት መስጫ ቦታ ነው::

3.2. *"ባለሥልጣን"* ማለት የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣንና የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) ናቸው::

3.3. *"ኦፕሬተር"* ማለት በመናኸሪያ የሚገለገል የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት ተመዝግቦ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የተሽከርካሪ ባለንብረት፣ ግለሰብ፣ ወይም ድርጅትና ቀጥረው የሚያሠሯቸውን አሽከርካሪዎችና ሌሎች ሠራተኞች ያካትታል::

3.4. *"የመናኸሪያ ባለቤት"* ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎችን ባለቤትነት ወይም የይዞታነት መብት ኖሮት የሚያስተዳድር ተቋም ነው::

3.5. *"የመናኸሪያ ግንባታ"* ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የሚገነቡ ወይም የተገነቡ ክፍሎች፣ አጥርና የመናኸሪያ ሜዳን ያካትታል::

3.6. *"የመናኸሪያ አስተዳደር"* ማለት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎችንና በውስጡ ያለውን የሰው ኃይል የመናኸሪያ ጥበቃና ጥገና በበላይነት ማስተዳደር ማለት ሲሆን፣ የሚያስተዳድረውን አካል ያካትታል::

3.7. *"የመናኸሪያ ተገልጋይ"* ማለት በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች አገልግሎት ለማግኘት የሚመጡ ተጓዦችና አጓጓዦች እንዲሁም መናኸሪያውን ሥነ-ሥርዓት የሚያስከብሩና የሚቆጣጠሩ የሕግ አስከባሪ አካላት ማለት ነው::

1.8 *"የአገልግሎት መስጫ ቢሮዎች"* ማለት በትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች የተገነቡ ማረፊያና መዝናኛ ክፍሎችና ስልዩ ልዩ አገልግሎት መስጫ እንዲያገለግሉ የተሠሩ ቢሮዎች ናቸው።

1.9 *"ረዳት"* ማለት በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ በማግኘት በሥራው ላይ የተሠማራ የአሽከርካሪ ረዳት ማለት ነው።

1.10 *"አሽከርካሪ"* ማለት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ያለውና የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጥ አውቶቡስ ወይም አውቶሞቢል የሚያሽከረክር ኦፕሬተር ማለት ነው።

1.11 *"ገንዘብ ተቀባይ"* ማለት በዕለትም ሆነ በቅድመ ትኬት አገልግሎት ከተጓዦች ገንዘብ የሚቀበል ስተቀበለው ገንዘብ ደረሰኝ የሚሰጥ በመናኸሪያ ውስጥና በትኬት ቢሮዎች ተመድቦ የሚሠራ ገንዘብ ሰብሳቢ ሠራተኛ ነው።

1.12 *"የሥምሪት ሠራተኛ"* ማለት የምዝገባ ፈቃድ የተሰጠው ማኅበርና የኦፕሬተር ብቃት ማረጋገጫ የተሰጠው የትራንስፖርት ድርጅት / ግለሰብ ቀጥር የሚያሰራው የሥምሪት አገልግሎት ሰጪ ሠራተኛ ማለት ነው።

1.13 *"የትራንስፖርት ማኅበር/ድርጅት/ግለሰብ"* ማለት በአዋጅ ቁጥር 468/97 አንቀጽ ክፍል ሁለት 12 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 መሠረት የተመዘገበ ማለት ነው።

1.14 *"የመናኸሪያ ደረጃ"* ማለት በዚህ መመሪያ መሥፈርት መሠረት ስሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት ተግባር ስሚሠሩ/ስተሠሩ መናኸሪያዎች የተሰጠ ደረጃ ነው።

1.15 *"የመናኸሪያ አገልግሎት ክፍያ"* ማለት በመናኸሪያ ስተሰጠ አገልግሎት፣ ኪራይ ወይም ሌላ ተመሣሣይ ክፍያ ነው።

4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዓላማ በሥራ ላይ ያሉና ወደፊትም በአዲስ የሚቋቋሙ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች ባለቤትነት ግንባታ፣ አስተዳደርና አጠቃቀም ወጥ በሆነ ስታንዳርድ የሚመሩበትን ሁኔታ በሀገሪቱ ሥራ ላይ ማዋልና ቀልጣፋ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል ነው፡፡

5. ግብ

በሀገሪቱ ያሉ መናኸሪያዎች አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃቸውን የጠበቁና የኅብረተሰቡን ፍላጐት የሚያረካ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፡፡

6. የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በመላ ሀገሪቱ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት በሚሰጡ መናኸሪያዎች፣ መናኸሪያዎችን በሚያስተዳድሩ የፌዴራልና የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) በሥራቸው በሚገኙ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችና በመናኸሪያው አገልግሎት በሚሰጡና በሚገለገሉ ማናቸውም አካላት ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

7. <u>የመናኸሪያ ባለቤትነት፣ ግንባታና አስተዳደር</u>

7.1. የመናኸሪያ ባለቤትነትን በተመለከተ

1. በዚህ መመሪያ በተጠቀሰው የደረጃ መሥፈርት (standard) መሠረት የአገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎችን በባለቤትነት ይዞ የሚያስተዳድረው የትራንስፖርት ባለሥልጣን ወይም የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቢሮዎች) መሆናቸውን፣ ይህንኑ ለማስፈፀም በየክልሉ ያሉትን መ/ቤቶች በማሣመን በራሱ የገቢ ደረሰኝ የሚሰበሰብበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡

2. ማንኛውም መናኸሪያ የ12 ሰዓት አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡ ሆናም መናኸሪያ ካለበት ከ50 እስከ 100 ኪ.ሜ ርቀት ላሉ አካባቢዎች እስከ ሚሸቱ 1 ሰዓት ድረስ አገልግሎት መስጠት ይኖርበታል፡፡

7.2. <u>በግንባታና ቦታ መረጣ የመንግሥትና የባለሀብቶች ድርሻ</u>

7.2.1. <u>የመንግሥት (የፌዴራል ወይም የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ድርሻ)</u>

ሀ. የከተማ ማስተር ኘላን በሚዘጋጅበት ጊዜ ተሣትፎ በማድረግ ለመናኸሪያ የሚውሉ ቦታዎች በአግባቡ በማስተር ኘላኑ እንዲካተቱ ማድረግ፣

ለ. መሥፈርቱን መሠረት በማድረግ ማስተር ኘላኑ በሚፈቅደው መሠረት ለመናኸሪያ መሥሪያ ቦታዎች ማዘጋጀት፣ ወይም የሚዘጋጁበትን ምቹ ሁኔታ መፍጠር፣

ሐ. የአካባቢውን ሕዝብ በማስተባበር ለመናኸሪያ ግንባታ በተሰጡት ቦታዎች መናኸሪያዎች እንዲከለሉ ደረጃውን በጠበቀ ሁኔታ እንዲገነቡ ማድረግ፣

መ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ መናኸሪያዎችን መገንባቱና በባለቤትነት ማስተዳደር፣

ሠ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በጨረታ አግባብ የመናኸሪያ ውስጥ የቁጥጥር ሥራና የሌሎች አገልግሎት ሥራዎችን out source በማድረግ መሠራት፣

ረ. የመናኸሪያ ቦታ ግንባታና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ (standard) ማዘጋጀትና በሥራ ላይ እንዲውል ማድረግ፣

ሰ. የግል ባለሀብቶች ሰራሳቸው ጠቀሜታ ደረጃውን የጠበቀ መናኸሪያ ለመገንባት ጥያቄ ሲያቀርቡ መርምሮ መፍቀድ::

7.2.2. የባለሀብቶች (የግል ባለሀብቶች፣ ማኅበራት፣ ድርጅት) ድርሻ

ሀ. መናኸሪያን በሚመለከት የወጡ የደረጃ መሥፈርቶችን ባሟላ ሁኔታ አገልግሎት መስጠት፣

ለ. ከመንግሥት በሚፈቀደው መሠረት አስፈላጊነቱ ሲታመንበት የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎችን መገንባት፣ ማስተዳደር፤

7.2.3. የመናኸሪያ ቦታ መረጣ ታሣቢዎች

ሀ. አካባቢው የሚታወቅበት ልዩ ሁኔታ በተለይም የአካባቢው የምርትና ኢንዱስትሪ ልማት ገፅታ፣ የማኅበራዊ እና ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ሁኔታ፣

ለ. የአካባቢው ባሕላዊ ዕሴት እና ማኅበራዊ ፍላጎት ደረጃ ማወቅ፣

ሐ. የከተማው ኘላን አቀማመጥ ሁኔታ እና የመንገዶች ቅያስ ለመናኸሪያው የሚያስገኘው ጥቅም እና የከተማውን የወደፊት ዕድገት መሠረት ማድረጉ፣

መ. በመናኸሪያ ግንባታ የቦታው የተፈጥሮ አቀማመጥ የሚያስከትለው የወጭ ግምት፣

ሠ. አስፈላጊ ነገሮችን በቅርበት ለማግኘትና የተገልጋዩን ፍላጐት ለማሟላት የተለያዩ የንግድ ድርጅቶች መኖራቸው ወይም በቀላሉ ሊስፋፉ የሚችሉ መሆኑ፣ ማለትም ለመንገደኞች የሚያስገኙት ተጨባጭ ጥቅም ካለ ማየት፣

ረ. የነዳጅ ማደያ አቅርቦትና የጋራዥ አገልግሎት ሁኔታ፣

ሰ. ለመንገደኛች እንቅስቃሴ አመች የደኅንነት ሁኔታና የተሟላ ጥበቃ ያለው መሆኑ፣ እንዲሁም የማደሪያ እና የማረፊያ ቦታ በተለይም ሆቴል እና ምግብ ቤት ስለመኖሩ እና ወደፊት ሊኖር ስለመቻሉ፣

ሸ. የሚመረጠው የመናኸሪያ ቦታ ሲስተም ቅየሳ አሬት ማዕዘን ላይ የሆነና ለሚገቡ እና ለሚወጡ መንገደኞች አመች እና አማካይ ቦታ መገኘቱ፣

ቀ. ለመናኸሪያው መቋቋም የአካባቢው ሕዝብ እና አስተዳደሩ ተነሣሽነት ያሳደረ መሆኑ፣

በ. አገልግሎት የሚሰጡ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች ብዛት እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ፣

ተ. የነዋሪው ሕዝብ ብዛት ታሣቢ ሲደረግ ይገባል፤

7.2.4. <u>የመናኸሪያዎች ደረጃና መሟላት የሚገባቸው መሥፈርቶች</u>

ሀ. በመላ ሀገሪቱ የሚገኙ ወደፊትም የሚገነቡ መናኸሪያዎች 3 ደረጃ ይኖራቸዋል:: እነሱም:

ደረጃ 1 የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች

ደረጃ 2 " " " " "

ደረጃ 3 " " " " "

ለ. የመናኸሪያ ደረጃ መሥፈርቶች መሠረት የሚያደርጉት ቀጥሎ የቀረበውን ዝርዝር መሠረት በማድረግ ይሆናል::

4.2 መሚሳት የሚገባቸው መሥፈርቶች በመናኸሪያ ደረጃ

ተ.ቁ	መሥፈርት	መለኪያ በቁጥር	ከፍተኛ ደረጃ 1 የክልልና የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች	መካከለኛ ደረጃ 2 የዞንና የወረዳ ከተሞች	አነስተኛ ደረጃ 3 የወረዳና ወረዳ ያልሆኑ ከተሞች
1	የሕዝብ ብዛት	ቁጥር	250,000	50-250,000	50,000
2	በቀን የሚስተናገዱ ተሽከርካሪዎች	በአንድ ጊዜ	እስከ 200	እስከ 100	እስከ 50
3	የመናኸሪያ ግቢ ስፋት	ካ.ሜ	25,000-45,000	15,000-30,000	10,000-15,000
4	የተሽከርካሪዎች ማቆሚያ ቦታ	ካ.ሜ	ለአንድ አውቶቡስ 75 ካ.ሜ ሥሌት	ለአንድ አውቶቡስ 75 ካ.ሜ ሥሌት	ለአንድ አውቶቡስ 75 ካ.ሜ ሥሌት
5	የግቢ አጥር	-	በግንብ ከ2 .50 ሜትር ከፍታ ከነገሪሱ ያሳነሰ	በግንብ ከ2.50 ሜትር ከፍታ ከነገሪሱ ያሳነሰ	በሽቦ የታጠረ
6	የግቢ ዓይነት	-	አስፋልት	አስፋልት	ምርጥ ጠጠር የለበሰ

7	**የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች ዓይነትና ስፋት**				
	ሀ. የምምሪት መስጫ ቢሮዎች ለአንድ ማኀበር/ድርጅት	በካ.ሜ	16	16	12
	ለ. የትምህርት መስጫና መሰብሰቢያ አዳራሽ		200	150	100
	ሐ. የጠፉ ዕቃዎች ማስቀመጫና ማስረከቢያ መጋዘን	"	50	30	20
	መ. የተንሾች ካፌቴሪያና ምግብ ቤት	"	450	280	150
	ሠ. የትኬት ማከማቻ፣ማደያ	"	95	56	42
	ረ. መፀዳጃ ክፍሎች /እንደ አስፈላጊነቱ የተከፋፈለ/		120	80	60
	ሰ. የተለያዩ አገልግሎት መስጫ ክፍሎች /የመረጃ መስጫና ሚኒ ሚዲያ፣ ሥነ-ሥርዓትና ፀጥታ አስከባሪዎች የመልዕክት መቀበያና ማሠራጫ.../	"	120	80	60
	ሸ. የIT መረጃ ማከማቻና ማጠናቀቂያ	"	በጥናት የሚወሰን	በጥናት የሚወሰን	በጥናት የሚወሰን
	ቀ. ለመንገደኞች ማረፊያና መጠባበቢያ	"	900	700	400
	በ. ኤሌክትሮኒክስ ቢል ቦርድ	-	✓	✓	-
	ተ. ሌሎች አገልግሎቶች/Facilities		በጥናት የሚወሰን		
	- ውኃ፣ መብራት		✓	✓	✓
	- ሚዛን		✓	✓	✓
	- የመንገደኞች ማረፊያ		✓	✓	✓
	- የቀሻሻ ማጠራቀሚያ		✓	✓	✓
	- የአደጋ መከላከያ		✓	✓	✓

ተ.ቁ	የሰው ኃይል ብዛትና የሥራ መደብ	መስኪያ በቀጥር	ከፍተኛ ደረጃ 1 የክልልና የአገሪቱ ዋና ዋና ከተሞች	መካከለኛ ደረጃ 2 የዞንና የወረዳ ከተሞች	አነስተኛ ደረጃ 3 የወረዳና ወረዳ ያልሆኑ ከተሞች
8	የሥራ ሂደት ባለቤት	በቀጥር	1	1	1
9	የምምረት ክትትልና ቁጥጥር ባለሙያ	"	ከ10 ያላነሱ	ከ7 ያላነሱ	5
10	ገንዘብ ሰብሳቢ	"	3	2	1
11	ሂሣብ ባለሙያ	"	3	2	1
12	የትምህርትና ቅስቀሣ ባለሙያ	"	6	4	2
13	የመረጃ አሰባሳቢና አጠናቃሪ ባለሙያ	"	4	2	1
14	የደኅንነትና ጥበቃ ሠራተኛ	"	16	8	4
15	የፅዳትና ግቢ ውበት ሠራተኛ	"	16	8	2
16	የሚዛንና የጠፉ ዕቃዎች ክትትል ባለሙያ	"	8	4	-
17	የIT ባለሙያ	"	4	3	1
18	የቢሮ ጥገና ክትትል ባለሙያ	"	4	3	1

ማሳሰቢያ:

የሰው ኃይል ዝርዝር የቀረበው ከትራንስፖርት ኦፕሬሽን ሥራ ጋር ስተያያዙ ተግባራት ብቻ ነው።

7.3. <u>አስተዳደርና አመራር</u>

7.3.1. <u>የፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣን፣ የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን ጽ/ቤቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

የፌዴራልና የክልል ትራንስፖርት ባለሥልጣን (ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች) በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሠጥተው መሥራት አለባቸው።

ሀ. ለመነሻ የተጠናውን የመናኸሪያ ግንባታ መሥፈርት መነሻ በማድረግ በከተሞች ለመናኸሪያ መሥሪያ ቦታዎች እንዲዘጋጁ በማስተር ኘላናቸቸው ውስጥ እንዲካተቱ በማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅርበት መሥራት፣

ለ. የአካባቢው ኅብረተሰብ በማስተባበር ለመናኸሪያ በተፈቀዱት ቦታዎች ደረጃውን የጠበቀ አጥር እና የአገልግሎት መስጫ ክፍሎች እንዲሠራ ማድረግና አገልግሎት ማስጀመር፣

ሐ. የተጀመሩ መናኸሪያዎችን ፍፃሜ እንዲያገኙ ማድረግ፣

መ. በሥራ ላይ ያሉ መናኸሪያዎች ያለባቸውን የፋሲሊቲ ችግር ለማቃለል በባለሙያ በማስጠናት የአገልግሎት ጥራት እና ደረጃ የሚሻሻልበትን ሁኔታ መፍጠር፣

ሠ. በመናኸሪያ ግንባታ ዙሪያ የሚሣተፉ ባለሀብቶችን ማበረታታትና የአቅም ግንባታ ድጋፍ መስጠት አለባቸው፣

ረ. የመናኸሪያዎችን አገልግሎት አሠጣጥ ለማሻሻል፣ ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ መመሪያዎችና አሠራሮችን ያወጣል፣ ተግባራዊ ያደርጋል፣

ሰ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመናኸሪያ ውስጥ ተሣትፎ ላላቸው አካላት የአቅም ግንባታ ሥልጠና ይሰጣል፣

ሸ. አስፈላጊ ሲሆን መናኸሪያዎችን አቅምና ችሎታ ላላቸው አካላት በውክልና ይሰጣል፣

ቀ. የመናኸሪያ ገቢ ተሰብስቦ ለመናኸሪያ ልማትና አገልግሎቶች የሚውልበት ሁኔታ ላይ ይሠራል። በተጨማሪም መናኸሪያውን

የሚያስተዳድረው አካል የመናኸሪያ አገልግሎት ክፍያ በትክክለኛው ታሪፍ መሠረት እያስከፈለ መሆኑን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

በ. ኃላፊነታቸውን በማይወጡ በመናኸሪያው ውስጥ አገልግሎት በሚሰጡ አካላት እና ሠራተኞች ላይ እንደየሥልጣን ገደቡ እርምጃዎች መውሰድ እና እንዲወሰድ ማድረግ፣

ተ. የመናኸሪያ አገልግሎትን በተመለከተ የሚመለከታቸውን ማስተባበር የሥምሪት እንቅስቃሴውን እና የትራንስፖርት አገልግሎቱን መከታተልና መቆጣጠር፣

ቸ. በልዩ ሁኔታ ውሣኔ የተሰጠባቸውን ጉዞዎች ተሽከርካሪዎች ካልሆኑ በስተቀር ማንኛውም የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪ በመናኸሪያ ውስጥ አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ፣

ነ. ተጓዦች ቅሬታ ሲኖራቸው ቅሬታቸውን በወቅቱ ተቀብሎ የማስተካከያ እርምጃ መውሰድ ለዚህም የሚረዳ በመናኸሪያ ውስጥ የሃሣብ መስጫ ሣጥን ገልጽ በሆነ ቦታ ማስቀመጥ የመረጃ ዲስክ ሠራተኞችን በመመደብ ማስተናገድ፣

ኘ. ሚኒ ሚዲያዎች፣ በቢል ቦርዶች፣ በብሮሸሮች እና በሌሎች ሥልቶች በመጠቀም ለኅብረተሰቡ ጠቃሚ መረጃዎችን መስጠት፣

ከ. መናኸሪያ አገልግሎት መስጫ ሰዓት መወሰን፣

ወ. መናኸሪያዎቹ ንጽሕና መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ዘ. ለመናኸሪያዎቹ የሥራ እንቅስቃሴ የሚረዱ የውስጥ ፋሲሊቲ እና የሰው ኃይል መሟላታቸውና ሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

ዠ. በመናኸሪያ ውስጥ የተገነቡ የሥራ ክፍሎች (ቢሮዎች) ከሴክተሩ ጋር ግንኙነት ላላቸው አካላት ብቻ አገልግሎት መስጠታቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

የ. መናኸሪያዎች ወቅታዊ ጥገና እንዲደረግላቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡ ለዚህም የሚረዱ አሠራር ቀይሶ ሥራ ላይ ያውላል፣

ደ. የተንዥን ደኅንነት ለመጠበቅ መጠለያዎች እና መቀመጫዎች በሚመለከታቸው አካላት እና ድጋፍ ሲሰጡ የሚችሉትን በማስተባበር እንዲሠሩ ማድረግ፤

7.3.2. <u>የፈፃሚ ሠራተኞች ተግባርና ኃላፊነት</u>

7.3.2.1. <u>የመናኸሪያ አስተዳደር ሥምሪት ክትትል ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በአግባቡ ሥራ ላይ መዋላቸውን ማረጋገጥ፣
2. ለተንዦች አገልግሎት የሚሆን መጠለያ፣ መቀመጫ፣ መፀዳጃ ቤቶችና ሌሎች አገልግሎቶች ሁሉ መሟላታቸውን ማረጋገጥ፣
3. በመናኸሪያው ውስጥ የሚሰጠው ሥምሪት በውድድር ላይ የተመሠረተ ደኅንነቱና ምቾቱ የተጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፣
4. ለመናኸሪያ የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎችና ሌሎች አገልግሎቶች እንዲሟሉ ማድረግ፣
5. መናኸሪያዎች በተዘጋጀላቸው ስታንዳርድ መሠረት እንዲገነቡ ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣
6. መናኸሪያው ውስጥ አገልግሎት የሚሠጡ ሠራተኞች ባጅና ዩኒፎርም ለብሰው እንዲሠሩ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
7. የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የመንገደኞች ጎዝ በሚዛን መዝነው ማስከፈላቸውን ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
8. ጫኝና አውራጆች ከመንገደኛው የአገልግሎት ክፍያ እንዳይቀበሉ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፣
9. የኦፕሬተርነት ብቃት ማረጋገጫ የምሥክር ወረቀት ያወጡ የተሽከርካሪ ባለንብረቶች ሥምሪት እንዲሠጡ ማድረግ፣
10. የየዕለቱን ሥምሪት ይከታተላል ፍላጐትና አቅርቦት የሚጣጣምበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
11. የሥምሪት መከታተያ ፎርማት በማዘጋጀት የተሽከርካሪ ባለንብረቶች የሚሠማሩበትን ፎርማቱን ይዘው ከመናኸሪያ እንዲወጡ ያደርጋል፣

12. መናኸሪዎዎች የተሻለ አሠራር እንዲኖራቸው ጥናት ያካሂዳል፣ በጥናቱ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፣

13. መናኸሪያዎች የተገነቡበትን ዓላማ እንዲወጡ የበኩሉን ጥረት ያደርጋል፣

14. የተሽከርካሪዎች አቋቋም ለአገልግሎት አሰጣጡ ምቹ በሆነና እንዲሁም ለተገልጋዩ በግልፅ በሚታይበት ሁኔታ እንዲሆን ማድረግ፣

15. በግቢ ውስጥ የሚያድሩና የሚንቀሳቀሱ ተሽከርካሪዎችን እንዲጠበቁ ማድረግ፣

16. በአገልግሎት ሰጭዎች፣ በትራንስፖርተሮች እና በተገልጋዮች መካከል የሚነሱ ግጭቶችን በአፋጣኝ መፍታት፣ ከአቅም በላይ ሲሆን፣ ለበላይ አካላት ማሣወቅ፣

17. በመናኸሪያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን መከታተል፣ መቆጣጠርና ችግሮች ሲከሰቱ ተገቢ የእርምት እርምጃ መውሰድ፣ ወይም ማስወሰድ፣

18. የተሣፋሪው ዕቃ በትክክል ተመዝና መብቱ ተጠብቆ መስተናገዱን መከታተልና ሕጉን ተላልፈው በተገኙት ላይ ክስ መመሥረትና እርምጃ ማስወሰድ፣

19. ኦፕሬተሮች በአግባቡ ዩኒፎርም እንዲለብሱ መከታተል፣ እርምጃ ማስወሰድ፣

20. ለአቅመ ደካማዎችና ለአካል ጉዳተኞች የተለየ እንክብካቤ የሚደረግበትን ምቹ ሁኔታ ማመቻቸት፣

21. ሌሎች ከሥራ ሂደቱ የሚሰጡ ተግባራቶችን ያከናውናል፡

7.3.3. የመናኸሪያ ትምህርትና ቅስቀሣ (የመረጃ) ባለሙያ

- ለስአገልግሎቱ ለተገልጋዩ ኅብረተሰብ መረጃ መስጠት፣ ለሰድሜ ባለጸጋዎች፣ ለአካል ጉዳተኞች ለሴቶች ልዩ ድጋፍና እገዛ እንዲደረግ መቀስቀስ፣
- መናኸሪያ ውስጥ የሚሰጡ አገልግሎቶች መረጃ መሰብሰብ፣ ማጠናቀርና አግባብነት ላላቸው አካላት ማስተላለፍ፣
- ከመናኸሪያ አሠራር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚፈቱበትን መንገድ ያመቻቻል፣
- መረጃ ሰጪ ጽሑፎችን በማዘጋጀት ለመንገደኛውና ለተሽከርካሪ ባለንብረቶች ያስተላልፋል፣
- ከመናኸሪያ አሠራር ጋር በተያያዘ መረጃ ይቀበላል፣ ያስተላልፋል፣
- የተለያዩ የመረጃ ማስተላለፊያ መሣሪያዎችን በመጠቀም ከሥራ ሂደቱና ከሌሎች የሥራ ሂደቱ የሚሰጡ መረጃዎችን ያስተላልፋል፣
- ሌሎች ከሥራ ሂደቱ የሚሰጡ ተግባራቶችን ያከናውናል፤

7.3.4. የመናኸሪያ ገንዘብ ሰብሳቢ

- የመናኸሪያ አገልግሎት ያገኙ የሕዝብ ማመላለሻ ተሽከርካሪዎች የአገልግሎት ክፍያ ይሰበስባል፣
- የተሰበሰበውን ገንዘብ በዕለቱ ባንክ ማስገባት፣
- ከባንክ ገንዘብ ማውጣትና የተለያዩ ክፍያዎችን መፈፀም፣
- የፋይናንስ ነክ ሪፖርቶች ማዘጋጀት፣
- የገንዘብ መሰብሰቢያ ደረሰኞች ታትመው ሥራ ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
- የፋይናንስ ነክ መረጃዎችንና ደረሰኞችን መጠበቅ፣
- ሌሎች ከሥራ ሂደቱ የሚሰጡ ተግባራቶችን ያከናውናል፤

7.3.5. የመናኸሪያ የሂሣብ ባለሙያ

- የመናኸሪያ የሂሣብ እንቅስቃሴ መዝገብ ላይ መመዝገብ፣

- ❖ ከሂሣብ ቋት (ሌዠር መዝገብ) ማቀናነስ፣
- ❖ ተሰብሳቢ ሂሣብ መከታተልና መቆጣጠር፣
- ❖ የሂሣብ ሚዛን (ትሪያል ባላንስ) ማዘጋጀት፣
- ❖ የዕለት ሣጥና ሂሣብ መሥራት/ቀጠሬ ማድረግ፣
- ❖ የባንክ ማስታረቂያ (Bank reconciliation) መሥራት፣
- ❖ ሠነዶችን ለምርመራ ዝግጁ ማድረግ፣
- ❖ ሌሎች ተዛማጅ ተግባርችን ማከናወን፡

7.3.6. የመናኸሪያ ደኅንነትና ጥበቃ ሠራተኛ ተግባርና ኃላፊነት

1. በየዕለቱ የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት እና በፎቶግራፍ የተደገፈ ማንነትን የሚገልጽ የደረት ባጅ ማንጠልጠል፣
2. በኅብረተሰቡ ዘንድ አስነዋሪ ድርጊቶች ናቸው የተባሉ ተግባራትን በመናኸሪያው ውስጥ አስመፈፀም፣
3. የግል ንጽሕናቸውን መጠበቅ፣
4. የመንገደኞችን ደኅንነት መጠበቅ፣
5. በመናኸሪያው ውስጥ የሥርቆት ወንጀል እንዳይፈፀም ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፣
6. በመናኸሪያው ውስጥ ሥርቀትና ዝርፊያ በተፈፀመ ጊዜ ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ማሣወቅ፣
7. መናኸሪያውን ሠላም የሚነሱ ጉዳዮች (መንገደኛ መጉተት፣ ማዋከብ፣ ጥሪ መጥራት፣ ወዘተ) ማስቆም፣
8. የተሸከርካሪ ባለንብረቶች የመናኸሪያ የአገልግሎት ሳይከፍሉ ከመናኸሪያ እንዳይወጡ ክትትልና ቁጥጥር ማካሄድ፣
9. የመናኸሪያውን በር ጠዋት 11:30 መክፈትና እንዲሁም ለሥምሪትና ከመስመር የሚገቡትን ተቀብሎ ማስተናገድ አስበት፣
10. መናኸሪያ ውስጥ የሚያድርን ተሽከርካሪ እና ተጭኖ የሚያድር ዕቃ በጥንቃቄ መጠበቅ፣

11. በመናኸሪያ ውስጥ ከተፈቀደላቸው ውጭ ዕቃ ተረክቦ አለማሣደር እና ከተጠቃሚው ለዕቃ ማሣደሪያ በግል የተለየ ክፍያ አለመጠየቅ፣

12. መንግሥት ለሚያወጣቸው የሥራ መመሪያዎች ተገዥ መሆን፤

7.3.7. የመናኸሪያ ፅዳትና ውበት ሠራተኛ ተግባርና ኃላፊነት

1. በፎቶግራፍ የተደገፈ ማንነትን የሚገልጽ የደረት ባጅ ማንጠልጠል እና በየዕለቱ የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት፣

2. በኅብረተሰቡ ዘንድ አስነዋሪ ድርጊቶች ናቸው የተባሉ ተግባራትን በመናኸሪያው ውስጥ አለመፈፀም፣

3. ተሣፋሪውን አለመሣደብ፣ አለመገላመጥ፣ አለመደበደብ፣ ለመደብደብ አለመሞከር፣

4. በየጊዜው የመናኸሪያውን ፅዳት መጠበቅ፣

5. በቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ የተጠራቀመውን ቆሻሻ በየጊዜው እየተከታተሉ ማስወገድ፣

6. መፀዳጃ ቤቶችን በየዕለቱ እየተከታተሉ ማጽዳት፣

7. የግል ንጽሕናቸውን መጠበቅ፣

8. ሌሎች ከሥራ ሂደቱ የሚሰጡ ተግባራትን ያከናውና፤

7.4. የግል ባለሀብቶች ማኅበራት እና ድርጅቶች ድርሻ

ሀ. በመንገድ ትራንስፖርት አገልግሎት ዘርፍ ያለውን የመናኸሪያ እጥረት ለመቅረፍ የተገልጋዩን ኅብረተሰብ፣ የግል ባለሀብቶችን የማኅበራትና ድርጅቶችን ተሣትፎ ማሣደግ፣

ለ. የራሣቸው የሆነ የተሽከርካሪ ማቆሚያ ማሣደሪያ መናኸሪያ በመገንባት ተሽከርካሪዎቻቸውን የመናኸሪያ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ በተጨማሪ

ሌሎችን ባለሀብቶች ወይም ድርጅቶች የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና ገቢ ማግኘት፤

7.5. <u>የትራንስፖርት ኦፕሬተሮች የመናኸሪያ አጠቃቀም</u>

1. የተጠቃሚውን ኅብረተሰብ ፍላጐት መሠረት ያደረገና በሠላማዊ ውድድር ላይ የተመሠረተ የትራንስፖርት የአገልግሎት መስጫ ሰዓት አገልግሎት መስጠት፣
2. ለአገልግሎቱ በተመደበው ሥፍራ ቆሞ መጫንና ማራገፍ አለበት፣
3. በመናኸሪያ ውስጥ ነዳጅና ዘይት መሙላት፣ የጥገና ሥራዎችን መሥራት፣ ጐማ መቀየር፣ ተሽከርካሪዎችን ማጠብ የለበትም፣
4. ኦፕሬተሮች የቴክኒክ ብቃት የሌላቸውን በቁልፍ የማይነሱ ተሽከርካሪዎችን መናኸሪያ ውስጥ ማስገባትም ሆነ ማቆም አይችሉም፣
5. ማንኛውም ኦፕሬተር በመናኸሪያ ውስጥ ላገኘው አገልግሎትና ለተከራያቸው ከፍሎች በወቅቱ ክፍያ መፈፀምና ሕጋዊ ደረሰኝ መቀበል፣ ማንኛውም ኦፕሬተር በዚህ መመሪያና በሥምሪት አፈፃፀም መመሪያው የተጠቀሱትን የመናኸሪያ አጠቃቀም ግዴታዎች አክብሮ መሥራት፤

<u>7.6 የዕቃ ጫንና አውራጅ ሰራተኞችን በተመለከተ:-</u>

ቀደም ሲል በዚህ መመሪያ የነበረው ሙሉ ለሙሉ ተሰርዞ ዕቃ ጫኝና አውራጅ ሠራተኞች በሙያ ተደራጅተውና ተጠሪነታቸው ለመናኻሪያ አስተዳደር ቡድን ሆኖ ከአገልግሎት ሰጪዎች ጋር የሚኖራቸው የሥራ ግንኙነትና የሚጠበቅባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተቀምጦ በአዲስ መልክ ራሱን በቻለ መመሪያ እንዲተካ ይደረጋል:: እስከዚያውም ደረስ ተጠሪነታቸው ለመናኻሪያ አስተዳደር ቡድን ሆኖ እየሰሩ ይቆያሉ::

9.3 <u>ሌሎች ሥነ-ሥርዓት አስከባሪዎች፣</u>

ቀደም ሲል በዚህ መመሪያ የነበረው ሙስ ስሙስ ተሰርዞ ሌሎች ምን-ምርዓት አስከባሪ ሠራተኞች በሙያ ተደራጅተውና ተጠሪነታቸው ስመናኻሪያ አስተዳደር ቡድን ሆና ከአገልገሎት ሰጪዎች ጋር የሚኖራቸው የሥራ ግንኙነትና የሚጠበቅባቸው ተግባርና ኃላፊነት በግልጽ ተቀምጦ በአዲስ መልክ ራሱን በቻለ መመሪያ እንዲተካ ይደረጋል:: እስከዚያውም ድረስ ተጠሪነታቸው ስመናኻሪያ አስተዳደር ቡድን ሆና እየሰሩ ይቆያሉ::

9.4 የአሽከርካሪዎች የመናኸሪያ አጠቃቀም

1. በመናኸሪያ የሚጠቀም ማንኛውም አሽከርካሪ በቂ ችሎታ ከተሟላ ጤንነት ጋር ያለው ሆና መገኘትና ለሚያሽከረክረው ተሽከርካሪ የሚመጥን ስደረጃው የብቃት ማረጋገጫ (መንጃ ፈቃድና) ሌሎች መረጃዎች አሟልቶ መገኘት አለበት፣
2. አሽከርካሪዎች ጉዞ ከመጀመራቸው በፊት የሚያሽከረክሩት ተሽከርካሪ የቴክኒክ ብቃቱ የተረጋገጠና ንጽሕናው የተጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ፣
3. የተሣፋሪውን ምቾትና ደኅንነት ለማረጋገጥ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት፣
4. ለተሣፋሪው ክብር መስጠት በተለይም አለመዝለፍ፣ አለመናቅ፣ ተሽከርካሪው መቆም በሚገባው ሥፍራ በማቆም የተሣፋሪውን ፍላጐት ባረጋገጠ አግባብ ማገልገል አለበት፣
5. በመናኸሪያ ውስጥ ተሽከርካሪ ሲበላሽ በአፋጣኝ መፍትሔ ማፈላለግና ለተሣፋሪው ሳይሠለች፣ ሳይጉላላ አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣
6. ለተጓዥ መንገደኞች ተገቢውን መረጃ መስጠት፣
7. በትራንስፖርት አካላት የሚወጡ ሕጐችን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን ጠብቆ መሥራት ይጠበቅበታል፡

9.5 ረዳቶች የሚያከናውኗቸው

1. ተሣፋሪዎች በወንበር ቁጥራቸው መሠረት እንዲቀመጡ ማድረግ፣
2. የመንገደኞች ዕቃ በተገቢው ሁኔታ ተጠብቆ እንዲጓዝ ማድረግ፣
3. የራሱንና የተሽከርካሪውን ንፅሕና የተሣፋሪው ምቾት በአግባቡ መጠበቅ፣
4. በጉዞ ወቅት የማረፊያ፣ የመመገቢያና የማደሪያ ሥፍራዎችን ለተሣፋሪው አስቀድሞ ማሣወቅ፣ የምግብና የሌሎች የጤና ችግሮች ሲያጋጥም መንገደኛውን በሚገባ መርዳት፣ ድጋፍ ማድረግ፣
5. የተዘጋጀውን የደንብ ልብስና መለያ ባጅ ለብሶ ተገቢውን አገልገሎት መስጠት፣

6. ተሣፋሪዎች ለአደጋ እንዳይጋለጡ የተሽከርካሪው በር መዘጋዱን ማረጋገጥ፣

7. ተሽከርካሪው ተሣፋሪው ጥና ከመንቀሣቀሱ በፊት የቴክኒክ አቋሙ ለጉዞ በቂ መሆኑን ማረጋገጥ፣

8. ሌሎች በሥምሪት መመሪያ ላይ የተገለፁትን ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት አለበት፤

9.6 ገንዘብ ተቀባዮች ኃላፊነት

1. ተሣፋሪዎች ለከፈሉት የማጓጓዣ ክፍያ ተገቢውን መረጃ በመሙላት ደረሰኝ መስጠት፣
2. የተሣፋሪዎች ዕቃ በትክክል ተመዝኖ ታግ መታሠሩን ማረጋገጥ፣ ተገቢ ክፍያ በማስከፈል ደረሰኝ መስጠት አለበት፣
3. ማንነቱን የሚገልጽ ባጅ እና የደንብ ልብስ ለብሶ መገኘት፣
4. የትራንስፖርት አገልግሎት ክፍያን አስመልክቶ መንግሥት ያፀደቀውን ታሪፍ ሥራ ላይ ማዋል፣
5. የተሽከርካሪዎች ደንንነትና የንፅሕና ሁኔታ ተጓድሎ በሚያይበት ጊዜ ለአሽከርካሪውና ለረዳቱ የማሣወቅ ሥራ መሥራት፣
6. ከሌሎች ከሥራ ባልደረቦቹ ጋር በመሆን ለተሣፋሪዎች ተገቢውን እንክብካቤ መስጠት፣
7. ሌሎች በሥምሪት አፈፃፀም መመሪያ ላይ የተገለፁ ተግባርና ኃላፊነቶች በአግባቡ መወጣት አለበት፤

9.7 የመናኸሪያ ፅዳት አጠባበቅ

መናኸሪያዎች የፀዱና የተገልጋዩን ዕርካታ የሚያስገኙ እንዲሆኑ በክልሉ በየደረጃው ተገቢው ጥበቃና ክትትል መደረግ ይኖርበታል:: ስለሆነም መናኸሪያዎችን ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው አካል የመናኸሪያዎችን ፅዳት መጠበቅ ይጠበቅበታል:: ይህንንም ለመፈፀም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ለባለሀብቶች፣ ለማኅበራት ወይም ለድርጅቶች በውል መስጠት (Out Source) ማድረግ ይቻላል::

9.8 የአገልግሎት ክፍያ

1. በፌዴራልም ሆነ በክልሎች መናኸሪያዎች በደረጃ ተለይተው ተዋቅረው የአገልግሎት ክፍያ መጠኑም በዚያው በደረጃቸው መሠረት ሆኖ ገቢውም ለመናኸሪያ አገልግሎት የሚውልበት ሁኔታ መመቻቸት አለበት::

2. በመናኸሪያ የሚጠቀም የተሽከርካሪ ኦፕሬተር በወጣው ሥሌት መሠረት ተገቢውን የመናኸሪያ ኪራይ መክፈል አለበት፣

3. የመናኸሪያ አገልግሎት አከፋፈል መጠንን በተመለከተ ተሽከርካሪዎች በአደሩበት መናኸሪያ አንድ ጊዜ ብቻ ማስከፈል አገልግሎት የሚሰጡ መናኸሪያዎችን ገቢ የሚቀንስ በመሆኑ አከፋፈሉ በአዳሪና በትራንዚት ሆኖ፣ በመናኸሪያ ደረጃዎችና በተሽከርካሪዎች የመቀመጫ ብዛት እንዲሆን የሚል ሆኖ አከፋፈሉም እንደሚከተለው ተዘርዝሯል:: ሆኖም ፌዴራል ትራንስፖርት ባለሥልጣንም ሆነ ክልሎች እንደራሣቸው ተጨባጭ ሁኔታ ሊያሻሽሉት ይችላሉ::

	ደረጃ 1-የሕዝብ መናኸሪያ		ደረጃ 2-የሕዝብ መናኸሪያ		ደረጃ 3-የሕዝብ መናኸሪያ	
ትራንዚት	አነስተኛ	ብር 3	አነስተኛ	ብር 2	አነስተኛ	ብር 2
	መለስተኛ	ብር 3	መለስተኛ	ብር 3	መለስተኛ	ብር 2
	ከፍተኛ	ብር 3	ከፍተኛ	ብር 4	ከፍተኛ	ብር 4
አዳሪ	አነስተኛ	ብር 4	አነስተኛ	ብር 3	አነስተኛ	ብር 2
	መለስተኛ	ብር 5	መለስተኛ	ብር 4	መለስተኛ	ብር 3
	ከፍተኛ	ብር 6	ከፍተኛ	ብር 5	ከፍተኛ	ብር 4

1. የአገልግሎት ክፍያ በተዘጋጀበት የጊዜ ሠሌዳ ተጠናቆ መክፈል አለበት፣
2. በመናኸሪያ ውስጥ የመገልገያ ቢሮ ኪራይ ከመናኸሪያው ባለቤት ጋር ባሳቸው ውል መሠረት ተፈፃሚ ይሆናል::

<u>ክፍል ሦስት</u>

8. <u>ልዩ ልዩ</u>

8.1. <u>በመናኸሪያ የመገልገል መብት</u>

8.1.1. ማንኛውም የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ለመስጠት የአገልግሎት ፈቃድ የተሰጠው ግለሰብ፣ ማኅበር፣ ድርጅት በመናኸሪያ ዕኩል የመገልገልና የመጠቀም መብት አለው፣

8.1.2. በተዘጋጀው የሥምሪት መርሀ-ግብር መሠረት አገልግሎት ለመስጠት መናኸሪያ እንዲገቡ የሚደረጉ ተሽከርካሪዎችና ሠራተኞች የደኅንነትና የጥበቃ ዋስትና የማግኘት፣

8.1.3. ቅሬታና አቤቱታ ሲኖር በአግባቡ የመሰማት (የመዳመጥ) እና ሕጋዊ መልስ የማግኘት፣

8.1.4. ለሰጡት የትራንስፖርት አገልግሎት ማግኘት የሚገባቸውን የክፍያ መጠን የማግኘት መብት አላቸው፣

8.2. ግዴታዎች

8.2.1. ማንኛውም ኦንሬተር ከመናኸሪያው አስተዳደር በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሚገለገሉበትን መናኸሪያ በአግባቡ መጠቀም፣

8.2.2. የመናኸሪያ አገልግሎትና የቤት ኪራዮች ክፍያ በገቡት ውል መሠረት በወቅቱ መፈፀም፤

8.3. የተገልጋይ መብቶች

8.3.1. ማንኛውም ተገልጋይ በመናኸሪያ ስመገልገል ሲመጣ መረጃ የማግኘትና ቅሬታውን በአግባቡ የማሰማት፣

8.3.2. ስፈፀመው የአገልግሎት ክፍያ ሕጋዊ ደረሰኝ የማግኘት፣

8.3.3. ያስምንም እንግልት ከመነሻ ቦታ መድረሻ ቦታው የመጓዝ፣

8.3.4. ያስጫነውን ዕቃ በትክክል የመረከብ፣

8.3.5. ከመነሻ እስከ መድረሻ በዕኩል መብት የመጓዝ፣

8.3.6. በመናኸሪያው ውስጥ በልዩ ልዩ ምክንያት አደጋ ቢከሰት ተገቢ ዕርዳታ የማግኘት መብት ይኖረዋል፤

8.3.7. በዕድሜ የገፉ የአካል ጉዳተኞች የሆኑ ሕፃናት ወይም ነፍሰ ጡሮች ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተሣፋሪዎች የአገልግሎት ቅድሚያ ድጋፍ ይደረግላቸዋል፡፡

8.4. የተገልጋዮች ግዴታ

8.4.1. ጉዞው ተጠናቆ መናኸሪያ እንዲደረሱ የመንገደኛና የዕቃ ትኬቱን መመለስ ዕቃውን በአግባቡ መረከብ፣

8.4.2. በመናኸሪያ ውስጥ አገልግሎት የሚሰጡ ሠራተኞችን አስመዝለፍ፣

8.4.3. ሌሎች በሥምሪት አሠራር መመሪያው የተጠቀሱትን ግዴታዎች መፈፀም ይጠበቅበታል፤

8.5. ቅጣት

ማንኛውም በሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያ የሚገለገል ኦንሬተር በዚህ መመሪያ መሠረት የተዘረዘሩትን አሠራሮች አክብሮ ካስሥራ፣ በሥምሪት አሠራር

መመሪያው የተቀመጠው የሥነ-ምግባርና ሥነ-ሥርዓት ጉድለት ቅጣት ተግባራዊ ይደረግበታል፡፡

8.6. <u>የተፈፃሚነት ወሰንና መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

8.6.1. ይህ መመሪያ በየትኛውም ደረጃ በሚገኙ የሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት መስጫ መናኸሪያዎች ውስጥ ተፈፃሚ ይሆናል፤

8.6.2. ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻል ይችላል፤

8.6.3. ይህ መመሪያ ከጥር/2005 ዓ.ም. ጀምሮ ሥራ ላይ ይውላል፡፡

የካቲት ቀን 2003 ዓ.ም.

ትራንስፖርት ባለሥልጣን

አዲስ አበባ፡፡